# ትግሉ ከቤተእምነቶች በላይ አገር የማዳን ትግል ነው!

ጥር 29 ቀን 2015ዓም(06-02-2023)

የኦርቶዶክስ ክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮችን ማዳን ማለት ተቋማቱን ማዳን ማለት ነው። የሁሉም እምነት ተከታይ የሆነው አማራ እንዳይረሳ አደራ!

የዛሬ 48 ዓመት ወያኔ ደደቢት በረሃ ሲገባ ዓላማ አድርጎ የያዘው የእምነት ተቋማትን በተለይም የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንንና የአማራውን ማህበረሰብ ለማጥፋት እንደነበረ ፣ሥልጣንም ላይ በተቀመጠበት የ27 ዓመት አገዛዙ እነዚህን በጠላትነት የፈረጃቸውን በግልጽና በድብቅ ሲያጠቃ እንደኖረ የሚካድ አይደለም።በእርሱ ጥፋተ እምነት የተጠመቁት አገር ጠል ሃይሎች፣ኦነግና ሌሎቹም ያንን የጥፋት ተልእኮ ተሸክመው በተግባር ሲፈጽሙ አሁን ካለንበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ባለፉት 32 ዓመታት ቤተክርስቲያን ሲያቃጥሉ፣ምእመናንን ሲያርዱ ኖረዋል።ከማህበረሰብም በኩል በሚከተለው እምነትና በጎሳ ማንነቱ የፈጇትን ዜጋ በተለይም ሊያጠፉት አቅደው የተነሱበትን  የአማራ ተወላጅ ስንት እንደገደሉ በአሃዝ ማስቀመጥ ይከብዳል።የገደሉበትን መንገድም ለመግለጽ ይዘገንናል።

ከአራት ዓመት ወዲህ በኦነግ ኦሕዴድ የተቃጠሉት ቤተእምነቶችና የታረዱት ምእመናን ከሌሎቹ ጊዜያቶች በቁጥርም በመጠንም ብዙ ናቸው።በሁለቱም ቤተእምነቶች ምዕመናን ላይ ከተሰነዘረው የማጥቃት ዘመቻ በዋናነት ሰለባ የሆነው አማራው ክርስቲያንና አማራው ሙስሊም ነው።ይህ የሚያሳዬው እምነቶቹና አማራው የተሳሰሩ መሆናቸውን ነው።አንዱ ከሌላው ተነጥሎ ያልተጠቃ መሆኑን ነው።ቤተእምነቶቹ ካለሰው ወና ቤቶች ናቸው።ሲያስከብራቸውና ሲያከብራቸው  የኖረው ምእመናኑ በዋናነት የአማራው ማህበረሰብ መሆኑ ሊካድ አይገባም።ለዚያም ነው አገር ለመበታተንና ለማፍረስ በተነሱት ቡድኖችና የውጭ ኣጋሮቻቸው አማራው እንደ ሃይማኖት ተቋማቱ ለኢትዮጵያ የጀርባ አጥንት ነው፤መጥፋትም አለበት ተብሎ የተፈረደበት።አማራ የኦርቶዶክስና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ብቻ ሳይሆን የካቶሊክና የፕሮቴሳንትም እምነቶች ተከታይ ነው።አማራውን ለማጥፋት ሲነሱ የነዚህንም እምነቶች  ተከታይ የሆነውን  ለማጥፋት ተነስተዋል ማለት ነው።

የኦነግ ኦሕዴድ አብዛኛው አባልና ደጋፊ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ መሆኑ አይካድም።ኦነግ ኦሕዴድ አማራውንና ሙስሊሙን ብቻ የሚያጠፋ መስሎ ከታዬውና ሃሌ ሉያና አሜን እያለ ካጨበጨበ በራሱ እምነት ተከታይም አማራው ላይ የሚፈጸመውን ግፍና  በደል ደጋፊና አበረታታች ሆኗል ማለት ነው።ይህ ደግሞ ከእውነተኛ  የፕሮቴስታንት እምነትና አስተምሮ ያፈነገጠና ሰይጣናዊ ምግባር የተጠናወተው አምልኮ ነው።የኦርቶዶክስ ተከታይ የሆነ የኦሮሞ ተወላጅም ኦሮሞ በመሆኑ ከኦነግ ብትር አላመለጠም።እንደ አማራው ተጨፍጭፏል።

ለዓመታት ሲካሄድ የቆዬውን አገርን የማፈራረስ ሴራ ከአምስት ዓመት ወዲህ በማጭበርበር ሥልጣኑን የተቆጣጠረው  የአብይ አህመድ  አሊ ቡድን የሚመራው የኦነግ ክንፍ በኦርቶዶክስ ተዋህዶና በእስልምና የእምነት ተቋማት ላይ የሚያደርገው ድፍረትና እብሪት የተመላበት ድርጊት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ገደቡን አልፎ በመምጣቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር በነቂስ ወጥቶ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ተቃውሞውን በመግለጽ ላይ ነው።የእምነት በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አባቶችና ምእመናን ግንባር ቀደሙን ትግል በመምራት የመስዋእትነት ጽዋን ለመቅመስ ተሰልፈዋል፣ገና ከጅምሩም በሙቶ የሚቆጠሩ ወጣቶችና ምእመናን አዛውንቶች የህይወት ዋጋ በመክፈል የሰማእታትነት ክብር ተቀዳጅተዋል።ሌላውም በነሱ ጎዳና ለመጓዝ ቆርጦ ተነስቷል።ላይመለስ

ቃል ገብቷል።ይህ ቁርጠኝነትና አብሮነት የሌሎች አገራትን የመንግሥትና የእምነት ተቋማትን ድጋፍና አብሮነት ለመጋበዝ በቅቷል።የሩስያ፣የሕንድ፣የአርመን፣የሶሪያ፣የግብጽና የኤርትራ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት ግንባር ቀደሞቹ ናቸው።ይህንን ተከትሎ በአዲስ አበባ የሚገኙት የውጭ አገር የመንግሥትና የዲፕሎማሲ ተጠሪዎች ለአብይ አህመድ መንግሥት ማስጠንቀቂያና ምክር በመስጠት ዝምታቸውን ሰብረዋል።ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ሕዝቡ በጽናትና በአንድነት በመቆሙ ነው።እስከዛሬ ድረስ ድምጻቸውን ያላሰሙት ችግሩን ሳያውቁት ቀርተው ሳይሆን የሕዝቡን አለመሰባሰብና ብርቱ ተቃውሞ አለማድረጉን በመመልከት ነበር።መቼም ምዕራባውያን የሕዝብን ስሜትና ጥንካሬ፣ እዬተከታተሉ ፣የመንግሥትንም ሁኔታ እዬመዘኑ አቋማቸውን እንደሚቀያይሩ ግልጽ ነው።አብይን አቅፈው፣ ደግፈው፣አሰልጥነው ለሥልጣን እንዳበቁት ከዚያም በተረፈ የፖለቲካ፣የዲፕሎማሲና የገንዘብ ድጋፍ እያደረጉለት መቆዬታቸውን ብናውቅም የአሁኑ ጅዋጅዌ ጨዋታቸውን ቀደም ሲል በምናውቀው እነሱም በማይክዱት መርህ አድርገው የሚመሩበት 'ቋሚ ወዳጅና ቋሚ ጠላት የለም' የሚለው እምነታቸው ለአሁኑ የመገለባበጥ አክሮባታቸው  መሠረት እንደሆነ ስለሚታወቅ ሊገርመን አይገባም።የአብይ ቡድን ከውድቀት ካንሰራራ ወይም ተወግዶ  ጠንክሮ ከሚወጣው ጋር አብሮ ላለመሰለፍ ይሉኝታ አያግዳቸውም።

የኦነግ ኦሮሙማው የአብይ ቡድን መሠረቱ ከተናጋ ፊታቸውን ለጊዜውም ቢሆን ወደ ሕዝቡ ቢመልሱ ሊደንቀን አይገባም።መጠንቀቅ ያለብን ዋናው ጉዳይ የነሱን ጥቅምና ፍላጎት የሚያስከብር፣የሕዝቡንና ያገራችንን ልዑላዊነትና ነጻነት አሳልፎ የሚሰጥ፣ባርያ የሆነ ተረኛ ቡድን እንዳይመጣብን ነው።

በተለይም የሩስያ ከሁሉም ቀድማ በአካል መልእክተኛ ልካ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጎን መቆሟ እነሱን ያጋለጣቸው ብቻም ሳይሆን ተቀባይነታቸውን የሚያሳጣ ሆኖ ስላገኙት የሚያደርጉት ውድድር እንደሆነም መዘንጋት አይኖርብንም።ማመን የዴሞክራሲ ሙብት ነው።አማኝን መግደል ዴሞክራሲን መግደል ማለት ነው።ለዴሞክራሲ እቆማለሁ ያለ አማኞች ሲገደሉና ወከባ ሲደርስባቸው ለምን ብሎ መጠዬቅና መቃወም የዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን የሰብአዊነት መገለጫ ነው።

ሌላው ጉዳይ ትግሉ ለኦርቶዶክስና ለእስልምና የእምነት ተቋማት ብቻ ሳይሆን አገር የማዳንም ትግል እንደሆነ ማሰብ ይገባል።ቤተእምነቶች ያለአገርና ምዕመናን ባዶ ቤቶች ናቸው፤አገርም ያለሕዝብ ባዶ መሬት ናት።ስለሆነም ትግሉ የሕዝቡንም ደህንነት ሊዘነጋው አይገባም።አሁን ተጠናክሮ የመጣው ሕዝባዊ ቁጣ በእምነት ተቋማቱ ዙሪያ ብቻ ሳይሆን በምእመናኑ ላይ በተለይም  በአማራው ላይ ያለውንም ማካተት ይኖርበታል። በሃይማኖት ትግል ወይም በሲኖዶሱ ጥያቄ ብቻ ላይ ተወስኖና ተሸፍኖ እንዳይቀር ሁሉም ሊያስብበት ይገባል።አሁንም አማራው እዬተጨፈጨፈ ነው። ህወሃትያውያኑና ኦነጋውያኑ  ትኩረቱ በቤተእምነቱ ዙሪያ ብቻ ላይ ነው በማለት ዋቢና ጠበቃ ያጣ ፣ የተረሳ የመሰላቸውን አማራውን እያረዱት ነው።ስለሆነም ቤተእምነቶቹ የሕዝቡን የመኖር ያለመኖር ጥያቄ ከተቋማቸው  መኖር ያለመኖር ጥያቄ ጎን ሊያዩት ይገባል። የአማራው መጨፍጨፍ ከቤተእምነቶች ውድመት ተነጥሎ አይታይም። በመለስተኛ ድል  እረክተው ከወንጀለኛው ቡድን ጋር መደራደር ማለት ደማቸውን ባፈሰሱት ወጣትና አዛውንት ምእመናን ደም ላይ መረማመድ ማለት ነው።ለዘላቂ ሰላምና ነጻነትም ሳይሆን ለዘለዓለማዊ ባርነት እጅ መስጠት ማለት ነው።ስለሆነም የእምነት አባቶች ባያደርጉት ይሻላል።እንጓዝበታለን ያሉትን የቀራኒዮን መንገድ ይከተሉ።

አሁን አጋጣሚውን በመጠቀም ወያኔና ኦነግ በያቅጣጫው ሃይላቸውን አጠናክረው አገር የመገነጣጠል የጥፋት ዘመቻቸውን ተያይዘውታል።ይህ  በሰሞኑ የቤተክህነት ጥያቄ ሳይድበሰበስና ችላ ሳይባል የትግሉ አካልና ዓላማ ሊሆን ይገባል። እስከዛሬ ድረስ ድምጻቸውን አጥፍተው የኖሩትና  አሁን  ላይ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ አንገቴን እሰጣለሁ ብለው የተነሱት የኪነት ባለሙያዎችና ምሁራን ለሰው ልጅ

ለሆነው፣ኢትዮጵያዊ ወገናቸው ሁሉ  በተለይም ለአማራው ተወላጅ  አጋርነታቸውን  “እኔም አማራ ነኝ !”  በሚለው መፈክር መግለጽ ይኖርባቸዋል።የትግል ግማሽ የለውምና!

የወንጀሉ ሁሉ ተጠያቂ የሆነውን በሥልጣን ላይ ያለውን ጸረ አገርና  ጸረ ሕዝብ የብልጽግና ቡድን እንደ መንግሥት ቆጥሮ፣ እውቅና ሰጥቶ ጥያቄ ማቅረብ ትክክል አይደለም።የሚመራበትንም የጥፋት ሰነድ ሕገ መንግሥት ብሎ በመቀበል እዬጠቀሱ መከራከርና ይከበር ማለት ሥርዓቱን አምኖ መቀበል ማለት ነው።ትግሉ እስከ ስርዓቱ ፍጻሜ ድረስ መዝለቅ አለበት።የካንሰርን በሽታ ቀርጠው በመጣል እንጂ በመዳበስ አያድኑትም!የዘር ፖለቲካም ከካንሰር የከፋ በሽታ ነው፤ መወገዝና መወገድ አለበት እንጂ፤በእርቅና በድርድር አይሻሻልም።

ሁለገቡ ትግል ይቀጣጠል! የአማራው የመኖር ጥያቄ የኦርቶዶክስና የእስልምና ተቋማት የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ አካል ነው!!

አገሬ አዲስ